# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

## የስርዓተፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ

የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት

ግንቦት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ለማካተት የወጣ

## መመሪያ ቁጥር 124/2009

የሴቶች መብት በተሻለ ሁኔታ ለማስከበር እንዲቻል፤ ሴቶችና ወንዶች እኩል መታየታቸውን እንዲሁም በሁሉም መስክ ሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ሚና እንዲጫወቱና በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት መዋቅሮች በሚካሄዱ የልማት ተግባራት እንዲሁም በፖሊሲ፣ በፕሮግራም፣ በፕሮጀክት፣ በመዋቅር፤ በአሰራር ስርዓት፣ በመመሪያ፣ በዕቅድ፣ በበጀት፣ በአፈፃፀም፣ ሪፖርት ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ እንዲካተት በማድረግ፤ ሴቶች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተት የልማት አጀንዳ አድርጎ በቁርጠኝነት መውሰዱ እና የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሁሉም የፌዴራልና የክልል መስተዳድር አስፈፃሚ አካላት ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት በተጨማሪ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ እንዲያካትቱ በአዋጅ ቁጥር 916/2008 የተሰጠው የወል ሥልጣን ለማስፈፀም መመሪያ በማስፈለጉ፤

ባለሥልጣኑ ይህንን የወል ሥልጣን ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት አኳያ ተግባራዊ ለማድረግ ቀደም ሲል የተዘጋጀው የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በማሻሻል በባለሥልጣኑ መ/ቤት መቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት አዋጁንና በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ሊያወጣ እንደሚችል ስለተደነገገ የባለሥልጣኑ ይህንን የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

"ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

1) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን የባለሥልጣኑን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለባለሥልጣኑ ተጠሪ የሆኑ መሥሪያ ቤቶችን ይጨምራል፣
2) "ሠራተኛ" ማለት በባለሥልጣኑ መ/ቤት በቋሚነት፣ ኮንትራትና በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ሲሆን የባለሥልጣኑን ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችንም ይጨምራል፣
3) "ቋሚ" ያልሆኑ ሠራተኞች" ማለት በባለሥልጣኑ መ/ቤት በጊዜያዊነትና ኮንትራት የተቀጠሩ ሠራተኞች ማለት ነው፣
4) "ሥርዓተ-ፆታ" ማለት ወንዶችና ሴቶች እንደየፆታቸው ከማህበረሰቡ የቀሰሙትን ባህሪና አመለካከት እንዲሁም ሚናና ኃላፊነትን የሚገልጽ ማለት ነው፤
5) "የፆታ እኩልነት" ማለት ሴቶችና ወንዶች ሰዎች በመሆናቸው ብቻ እኩል ተፈጥሮአዊ መብቶችና ግዴታዎች ያሉባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማለት ነው፡፡
6) "ፆታዊ ሚዛናዊነት" ማለት የሴቶችና የወንዶች ተሳታፊነት፣ ተጠቃሚነት ኃላፊነትና ተጠያቂነት ሚዛናዊ እንዲሆን ማድረግ ማለት ነው፤
7) "የሶስትዮሽ ሚና" ማለት የሴቶች የእናትነት ፤የአምራችነትና የማህበረሰብ ተሳትፎ ሚና ማለት ነው፤
8) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትንም ፆታ ያገለግላል፤

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ መሥሪያ ቤቶች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

በዓለም፣ በአህጉርና በአገር አቀፍ ደረጃ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በሚመለከት የወጡ ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ፓኬጆች ከባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት አኳያ እንዲካተት በማድረግ የሴቶች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በየደረጃው የሚገኙ አመራርና ሠራተኞች ቁርጠኛ ኃላፊነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ተግባርና ኃላፊነት

5. <u>የባለሥልጣኑ የበላይ ሥራ አመራር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የባለሥልጣኑ የበላይ ሥራ አመራር አካላት የባለሥልጣኑ ህጎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና መመሪያዎች፣ የአሰራር ሥርዓቶች ሀሳብ የማመንጨት የባለሥልጣኑን ተግባራት በስትራቴጂክ ዕቅድ የመምራት ኃላፊነት አለበት፡፡

2) ከሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተት አኳያ ተግባርና ኃላፊነታቸው፡-

(ሀ) የባለሥልጣኑ መ/ቤት አጠቃላይ አቅጣጫ ሰጪ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሲዘጋጁ የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፣

(ለ) የባለሥልጣኑ መ/ቤት ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴት፣ ዓላማ፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲዘጋጁ ማድረግ፣

(ሐ) በባለሥልጣኑ መ/ቤት በፖሊሲ፣ ፕሮግራም፣ ፕሮጀክት መዋቅር፣ አሰራር ስርዓት፣ መመሪያ፣ ዕቅድና በጀት ዝግጅትና በአፈፃጸምና ሪፖርት በክትትልና ግምገማ ወቅት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ

እንዲካተተ ማድረግ፣

(መ) በባለሥልጣኑ መ/ቤት በከፍተኛ መካከለኛና ዝቅተኛ የአመራር ደረጃ የሴቶች ተሳታፊነት ለማሳደግ፤ አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ ፤

(ሠ) በባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዕቅድ፣ በጀትና ሪፖርት በክትትልና ግምገማ ሥርዓት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ መካተቱን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

(ረ) በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በማሳደግ የፆታ እኩልነት እንዲረጋገጥ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ኃላፊነት እንዲኖር ማድረግ፤

6. <u>የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ዋና ዓላማ አጠቃላይ የባለሥልጣን መ/ቤቱን አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች በመምራትና በስሩ ያሉትን ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በማስተባበር አስፈላጊውን የድጋፍና ክትትል ሥራዎች በማከናወን ዘመናዊ የግብርና ቀረጥ አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ሲሆን፤

2) ከሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተት አኳያ ተግባርና ኃላፊነቱ፦

(ሀ) የባለሥልጣኑ አመራሮችና ሠራተኞች ሴቶችን የሚመለከቱ የወጡ፣ የተሻሻሉ ህጐች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች፣ ፕሮግራሞችና፣ ፓኬጆች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

(ለ) በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች በፖሊሲ፣ ፕሮግራም ፕሮጀክት፣ መዋቅር፣ አሰራር ሥርዓት፣ መመሪያ፣ ዕቅድ በጀት ዝግጅት እና አፈፃጸም ሪፖርት በክትትልና ግምገማ ስርዓት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ እንዲካተት ማድረግ፤

(ሐ) የዋና ዳይሬክተር አማካሪዎች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በዘርፎች፣ ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን የምክር፣ ክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤

Ethiopian Revenues and Customs ... Records & Documentation

(መ) ባለሥልጣኑ በሥርዓተ-ፆታ [illegible]

የሚያስፈልግ በቂ በጀት እንዲመደብ ማድረግ፤

(ሠ) የባለሥልጣኑ የሥርዓተ-ጾታ ማካተቻ ጉዳይ በዕቅድ፣ በበጀት የተደገፈ እና በጊዜ የተገደበ የሚመዘንና፣ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣

(ረ) በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሥራቸው የሚገለገሉባቸው ቅፆችና ቼክሊስቶች ሲዘጋጁና ሲቀረፁ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሰ) በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚቋቋሙ ግብረ-ሀይሎችና ኮሚቴዎች የሴቶችን ተዋፅኦ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፣

(ሸ) በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሚከናወኗቸው ተግባራት የሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የክትትል፣ ድጋፍ እና የግምገማ ሥራዎች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ቀ) በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚታቀዱና የሚሰጡ ሥልጠናዎች የሴቶችና የወንዶችን ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፣

(በ) በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚጠኑ ጥናቶች ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ተ) ለባለሥልጣኑ ሴት ሰራተኞች የአመራርና ውሳኔ ሰጭነት አቅምና ብቃትን የሚያሳድጉ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ማድረግ፤

(ቸ) በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴት ሠራተኞችን የመረጃ ቴክኖሎጂ ክፍተት በመለየት ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ኀ) ለባለሥልጣኑ ባለድርሻ አካላት የሚላኩ ዕቅዶች፣ ሪፖርቶች መረጃዎች በፆታ ተለይተው እንዲዘጋጁና እንዲደረጁ ማድረግ፤

(ነ) በባለሥልጣኑ ኢንቨስትመንት ለማበረታታት የሚደረግ ድጋፍና

ክትትሎች የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ኘ) የባለሥልጣኑ ሴት ሠራተኞች እና ግብር ከፋይ ሴቶች በሥነ ምግባር ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፤

(አ) የባለሥልጣኑ ሴት ሠራተኞች እና ግብር ከፋይ ሴቶች የሥነ ምግባር ሁኔታቸው በየጊዜው እንዲጠና ማድረግ፤

(ከ) በባለሥልጣኑ ሴት ሠራተኞች ላይ የሚደርሱ ፆታዊ ጥቃትና ትንኮሳ የሥነ-ምግባር እና የዲስፕሊን ችግር በመሆኑ ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ፤

(ኸ) በባለሥልጣኑ ሴት እና ወጣት ሠረተኞች ጉዳይ ተጠሪዎች የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበት የጋራ መድረክ እንዲዘጋጅ ማድረግ፤

(ወ) የባለሥልጣኑ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ መሆኑ በክዋኔ ኦዲት እንዲፈተሽ ማድረግ፤

(ዐ) በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሥራ፣ የሰው ሀይል የሥልጠና መረጃዎች በፆታ ተለይተው እንዲያዙና እንዲደራጁ ማድረግ፤

7. <u>የፌዴራል አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ</u>

1) የፌዴራል አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ ዋና ዓላማ በስሩ ያሉትን ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በመምራትና በማስተባበር አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ዘመናዊ የታክስ አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ገቢን በብቃት እንዲሰበሰብ ማድረግ ሲሆን፤

2) ከሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተት አኳያ ተግባርና ኃላፊነቱ፡-

(ሀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የፖሊሲና እስትራቴጂ ሀሳቦች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ለ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሚከናወኑ ተግባራት የሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ በጀቶች፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ ክትትል፣ ድጋፍና፣ የግምገማ ሥራዎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

(ሐ) የዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አማካሪዎች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በዘርፎች፣ በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን የምክር የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤

(መ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የስልጠና ፕሮግራሞች የሴቶችና የወንዶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሠ) በዘርፍ፣ በዳይሬክቶሬቶችና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየደረጃው ለሚገኙ ግብር ከፋይ ሴቶች በግብር ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ረ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሥራቸው የሚገለገሉባቸው ቅፆችና ቼክ ሊስቶች ሲዘጋጁና ሲቀረፁ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሰ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚቋቋሙ ግብረ-ኃይሎችና ኮሚቴዎች የሴቶችን ተዋፅኦ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤

(ሸ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚያዙ የሥራ፣ የሰው ሀይል፣ የሥልጠናና የግብር ከፋይ መረጃዎች በፆታ ተለይተው እንዲደራጁና እንዲያዙ ማድረግ፤

(ቀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴትና ወንድ ሠራተኞችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፤

(በ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚጠኑ ጥናቶች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲጠኑ ማድረግ፤

(ተ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሴት ሠራተኞች ለተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚያስፈልጋቸውን የሙያ ብቃትና



የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
The Federal Democratic Republic of Ethiopia

ክህሎት ለማሳደግ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ቸ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴት ሠራተኞችን የመረጃና ቴክኖሎጂ ክፍተት በመለየት አጠቃቀማቸውን ለማሻሻል ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ኀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ለማሻሻል ምርጥ ተሞክሮዎች ሲቀመሩና ሲስፋፉ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ እንዲያገናዝቡ ማድረግ፤

(ነ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የግብር ከፋዮች መረጃ በደረጃና በፆታ ተለይቶና ተተንትኖ እንዲደራጅና እንዲያዝ ማድረግ፤

8. <u>የአዲስ አበባ አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ</u>

(1) የአዲስ አበባ አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ ዋና ዓላማ በስሩ ያሉትን ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በመምራትና አስፈላጊውን የድጋፍና ክትትል ሥራዎች በማከናወን ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት አስተዳደሩን ገቢ በብቃት እንዲሰበሰብ ማድረግ ሲሆን፤

(2) ከሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተት አኳያ ተግባርና ኃላፊነቱ፡-

(ሀ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሀሳቦች፣ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ለ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሚከናወኑ ተግባራት የሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ በጀቶች፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የክትትልና ድጋፍ፣ የግምገማ ሥራዎች የሥርዓተ- ፆታን ጉዳይ በማካተት እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

(ሐ) የዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አማካሪዎች የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በዘርፉ፤ በዳይሬክቶሬቶችና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ተግባራዊ እንዲሆን የምክር፣ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤

(መ)በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የሥልጠና ፕሮግራሞች የሴቶችና የወንዶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሠ)በዘርፉና በስሩ የሚገኙ በዳይሬክቶሬቶችና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየደረጃው ለሚገኙ ግብር ከፋይ ሴቶች በግብር ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ረ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሥራቸው የሚገለገሉባቸው ቅፆችና ቼክሊስቶች ሲዘጋጁና ሲቀረፁ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሰ) በዘርፉና በሥሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚቋቋሙ ግብረ-ኃይሎችና ኮሚቴዎች የሴቶችን ተዋፅኦ ትኩረት እንዲሰጥበት ማድረግ፤

(ሸ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚያዙ የሥራ፣ የሰው ሀይል፣ የሥልጠናና የግብር ከፋይ መረጃዎች በፆታ ተለይተው እንዲደራጁና እንዲያዙ ማድረግ፤

(ቀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴትና ወንድ ሠራተኞችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፤

(በ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚጠኑ ጥናቶች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲጠኑ ማድረግ፤

(ተ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሴት ሠራተኞች ለተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚያስፈልጋቸውን የሙያ ብቃትና ክህሎት ለማሳደግ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ቸ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴት ሠራተኞችን የመረጃና ቴክኖሎጂ የዕውቀትና የአጠቃቀም ክፍተታቸውን በመለየት ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ኀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ለማሻሻል ምርጥ ተሞክሮዎች ሲቀመሩና ሲስፋፉ የሥርዓተ-ፆታ

ጉዳይን እንዲያገናዝቡ ማድረግ፣

(ነ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የግብር ከፋዮች መረጃ በደረጃና በያታ ተለይቶና ተተንትኖ እንዲደራጅና እንዲያዝ ማድረግ፤

9. <u>የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ዋና አላማ በስሩ የሚገኙትን ዳይሬክቶሬቶችና ቅ/ጽ/ቤቶችን በመምራትና አስፈላጊውን የድጋፍና ክትትል ስራዎች በመስራት ዘመናዊ የቀረጥ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለደንበኞች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት ገቢን በብቃት እንዲሰበሰብ ማድረግ ሲሆን፤

2) ከሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተት አኳያ ተግባርና ኃላፊነቱ፦

(ሀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የፖሊሲና የስትራቴጂ ሃሳቦች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ለ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሚከናወኑ ተግባራት የሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ በጀቶች፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ ክትትል፣ ድጋፍና የግምገማ ሥራዎች የሥርዓት- ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

(ሐ) የዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አማካሪዎች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በዘርፎች፣ ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን የምክር፤ ክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤

(መ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የሥልጠና ፕሮግራሞች የሴቶችና የወንዶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሠ) በዘርፉና፣ በዳይሬክቶሬቶችና በቅ/ጽ/ቤቶች በየደረጃው ለሚገኙ አስመጪና ላኪ ቀረጥ ከፋይ ሴቶች በቀረጥ አወሳሰንና አሰራር ሥርዓት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፤

(ሬ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሥራቸው የሚገለገሉባቸው ቅፆችና ቼክሊስቶች ሲዘጋጁና ሲቀረፁ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን እንዲያገናዝቡ ማድረግ፤

(ሰ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚቋቋሙ ግብረ-ኃይሎችና ኮሚቴዎች የሴቶችን ተዋፅኦ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤

(ሸ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚያዙ የሥራ፣ የሰው ሀይል፣ የሥልጠና፣ የአስመጪና ላኪ ነጋዴዎች እና የጉምሩክ አስተላላፊዎች መረጃ በጾታ ተለይተው እንዲደራጁና እንዲያዙ ማድረግ፤

(ቀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴትና ወንድ ሠራተኞችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፤

(በ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚጠኑ ጥናቶች የስርዓተ-ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲጠኑ ማድረግ፤

(ተ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሴት ሠራተኞች ለተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚያስፈልጋቸውን የሙያ ብቃትና ክህሎት ለማሳደግ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፣

(ቸ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴት ሠራተኞችን የመረጃና ቴክኖሎጂ የዕውቀትና የአጠቃቀም ክፍተታቸውን በመለየት ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ኀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የቀረጥ አስተዳደር ስርዓት ለማሻሻል ምርጥ ተሞክሮዎች ሲቀመሩና ሲስፋፉ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ነ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የአስመጪና ላኪ ቀረጥ ከፋዮች መረጃ በደረጃና በፆታ ተለይቶና ተተንትኖ እንዲደራጅና እንዲያዝ ማድረግ፣

10. <u>የህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶችንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለቀናጅቶ

በመምራትና በማስተባበር፣ የታክስና የጉምሩክ ወንጀሎችን በመከላከል የታክስ ሕግ ተገዥነትን በማሳደግ ገቢ በብቃት እንዲሰበሰብ ማድረግ ሲሆን፤

2) ከሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተት አኳያ ተግባርና ኃላፊነቱ:-

(ሀ)በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የፖሊሲና የስትራቴጂ ሀሳቦች፣ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ለ) የባለሥልጣኑ መ/ቤት የግብርና ቀረጥ ህጎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ሲረቀቁና ሲዘጋጁ የሴቶች ተሳትፎ ትኩረት እንዲሰጥበት ማድረግ፤

(ሐ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሚከናወኑ ተግባራት የሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ በጀቶች፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የክትትልና ድጋፍ እና የግምገማ ሥራዎች የሥርዓተ- ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

(መ) የዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አማካሪዎች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በዘርፎች፣ በዳይሬክቶሬቶችና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን የምክር፣ ክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤

(ሠ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የስልጠና ፕሮግራሞች የሴቶችና የወንዶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ረ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሥራቸው የሚገለገሉባቸው የሥራ ቅፆችና ቼክሊስቶች ሲዘጋጁና ሲቀረፁ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሰ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚቋቋሙ ግብረ-ኃይሎችና ኮሚቴዎች የሴቶችን ተዋፅኦ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤

(ሸ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚያዙ የሥራ፣ የሰው ሀይል፣ የሥልጠናና በዘርፉ አገልግሎት የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች መረጃ በፆታ ተለይተው እንዲደራጁና እንዲያዙ ማድረግ፤

(ቀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴትና ወንድ ሠራተኞችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፤

(በ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚጠኑ ጥናቶች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲጠኑ ማድረግ፤

(ተ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሴት ሠራተኞች ለተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚያስፈልጋቸውን የሙያ ብቃትና ክህሎት ለማሳደግ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ቸ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴት ሠራተኞችን የመረጃና ቴክኖሎጂ የዕውቀትና የአጠቃቀም ክፍተታቸውን በመለየት ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ኀ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የታክስ ህግ ተገዥነት ሥርዓት ለማሻሻል ምርጥ ተሞክሮዎች ሲቀመሩና ሲስፋፉ የሥርዓተ ፆታን ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ነ) በዘርፉና በስሩ በሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የግብር ከፋዮች የህግ ተገዥነት መረጃ በደረጃና በፆታ ተለይቶና ተተንትኖ እንዲደራጅና እንዲያዝ ማድረግ፤

## 11.የሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ ተግባርና ኃላፊነት

1) የባለሥልጣኑን የሰው ሀብት ሥራ አመራር፣ የለውጥ ትግበራ፣ የጥናትና ልማት፣ የትምህርትና ግንኙት፣ የደንበኞች አገልገሎት የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራዎችን በመምራት በማስተባበርና ሀብት በመመደብ ለደንበኞች ፍትሀዊ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት ገቢን በብቃት እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤

2) ከሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተት አኳያ ተግባርና ኃላፊነቱ፡-

(ሀ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የፖሊሲና የስትራቴጂ ሀሳቦች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ለ)በዘርፉና በሥሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሚከናወኑ ተግባራት የሚዘጋጁ

ዕቅዶች፣ በጀቶች፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የክትትልና ድጋፍ እና የግምገማ ሥራዎች የሥርዓተ- ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

(ሐ) የዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አማካሪዎች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በዘርፎች፣ በዳይሬክቶሬቶችና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን የምክር፣ ክትትልና የድጋፍ ሥራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤

(መ)በዘርፉና በሥሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚዘጋጁ የሥልጠና ፕሮግራሞች የሴቶችና የወንዶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሠ)በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለሥራቸው የሚገለገሉባቸው የሥራ ቅፆችና ቼክሊስቶች ሲዘጋጁና ሲቀረፁ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ረ) በባለሥልጣኑ መ/ቤት የቅጥር፣ ሥልጠና፣ ምደባ፣ ደረጃ ዕድገትና ዝውውር መመሪያዎች የአሰራር ሥርዓቶችና አደረጃጀቶች የሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ትኩረት ሰጥተው እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

(ሰ) በባለሥልጣኑ መ/ቤት በዝቅተኛ የሥራ ደረጃና ትምህርት የሚገኙ ሴት ሠራተኞች የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማሳደግ የሥራ ፈጠራ ሥልጠናና ብድር እንዲመቻቹላቸው ማድረግ፤

(ሸ) በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሰው ኃይል መረጃ በጾታ፣ ዕድሜ፣ ጋብቻ ሁኔታ፣ ትምህርት ደረጃና መስክ፣ አገልግሎት ዘመን፣ ሥራ መደብ እና በኃላፊነት ደረጃ፣ ተለይተው እንዲደራጁና እንዲያዙ ማድረግ፤

(ቀ) በባለሥልጣኑ መ/ቤት በዝቅተኛ ሥራና የትምህርት ደረጃ ለሚገኙ ሴት ሠራተኞች የትምህርትና ሥልጠና ዕድል የሚያገኙበት ስትራቴጂ በመቅረፅ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤

(በ) በባለሥልጣኑ መ/ቤት በሀገር ውስጥና በውጪ አገር በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚሰጡ የትምህርትና ሥልጠና ዕድሎች የሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤

(ተ) በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚዘጋጁ መጽሔቶች፣ ብሮሸሮች፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በቴሌቭዥን እና በድረ-ገጽ የሚተላለፉ ፕሮግራሞች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ቸ) በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በስርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራትና የሚተላለፉ መሪ ቃሎች በሚድያ (በኤሌክትሮኒክስና ህትመት) የማሳወቅ ስራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤

(ኀ) የባለሥልጣኑ ሴት ሠራተኞች ከትዳር አጋሮቻቸው አብረው ለመኖርና ህፃናት ልጆቻቸውን ለመንከባከብና ለማሳደግ የሚያቀርቡት የሥራና የቦታ ዝውውር ጥያቄ ልዩ ድጋፍና ትኩረት እንዲሰጥበት ማድረግ፤

(ነ) የባለሥልጣኑ ሴት ሠራተኞች በተፈጥሮ የተሰጣቸው ልጅ የመውለድና የማሳደግ ኃላፊነት ከሥራቸው አጣጥመው ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸው በጥናት የተደገፈ የህፃናት መቆያ አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

(ኘ) በባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሠራተኞች የሚገዙ የሥራ ልብስ፤ ጫማና ሌሎች መገልገያ ዕቃዎች የሴቶችን ፍላጎት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(አ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚቋቋሙ ግብረ-ኃይሎችና ኮሚቴዎች የሴቶችን ተዋፅኦ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ፤

(ከ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚያዙ የሥራ፣ የሰው ሀይል፣ የሥልጠናና በዘርፉ አገልግሎት የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች መረጃ በጾታ ተለይተው እንዲደራጁና እንዲያዙ ማድረግ፤

(ኸ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴትና ወንድ ሠራተኞችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፤

(ወ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚጠኑ ጥናቶች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን በማካተት እንዲጠኑ ማድረግ፤

(ዐ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሴት ሠራተኞች ለተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚያስፈልጋቸውን የሙያ ብቃትና ክህሎት ለማሳደግ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ዘ) በዘርፉና  በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የሴት ሠራተኞችን የመረጃና ቴክኖሎጂ የዕውቀትና የአጠቃቀም ክፍተታቸውን በመለየት  ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፣

(ገ) በዘርፉና በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ለማሻሻል ምርጥ ተሞክሮዎች ሲቀመሩና ሲስፋፉ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን እንዲያካትቱ  ማድረግ፣

(የ) በዘርፉና  በስሩ የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች ለውስጥና ለውጭ ደንበኞች የተሰጡ አገልግሎቶች መረጃ በፆታ ተለይቶና ተተንትኖ እንዲደራጅና እንዲያዝ ማድረግ፣

12. <u>የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዋና ዓላማ በስራቸው የሚገኙ የሥራ ሂደቶችንና የሥራ ቡድኖችን በመምራትና በማስተባበር እና ዘመናዊ የቀረጥና የታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ ለተገልጋዮች ፍትሃዊና ቀልጣፋ አገልግሎት  በመስጠት የግብር ስወራ፣ ማጭበርበርና ኮንትሮባንድን በመከላከል ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት መሰብሰብ ሲሆን፤

2) ከሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ማካተት አኳያ ተግባርና ኃላፊነታቸው፡-

(ሀ) በቅ/ጽ/ቤቱና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ክፍሎች የሚዘጋጁ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሀሳቦች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅዶች የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ለ) በቅ/ጽ/ቤቱና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች ለሚከናወኑት ተግባራት የሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ በጀቶች፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የክትትልና ድጋፍ፣የግምገማ ሥራዎች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን በማካተት እንዲዘጋጁ ማድረግ፣

(ሐ) በቅ/ጽ/ቤቱ የሴቶችና የወጣቶች ጉዳይ መዋቅር  በአደረጃጀትና አሰራር ያለውን ክፍተት በመለየት በቂ የሰው ኃይልና በጀት በመመደብ ውጤታማ እንዲሆን  ማድረግ፣

(መ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዝቅተኛ የሥራ ደረጃና ትምህርት የሚገኙ ሴት ሠራተኞች የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለማሳደግ የስራ ፈጠራ ስልጠናና ብድር እንዲመቻቹላቸው ማድረግ፤

(ሠ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚደረጉ የሥራ ስምሪቶች ፆታዊ ተዋጽኦን እንዲያገናዝቡ ማድረግ፤

(ረ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሠራተኞች የሚገዙ የሥራ ልብስ ጫማና ሌሎች መገልገያ ዕቃዎች የሴቶችን ፍላጎት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ሰ) የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሠራተኛ መተዳደሪያ ደንብ የቅጥር፣ ስልጠና፣ ዕድገትና ዝውውር መመሪያዎች በቅ/ጽ/ቤቱ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ትኩረት በመስጠት ተግባራዊ ማድረግ፤

(ሸ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የሚዘጋጁ የሥልጠና ፕሮግራሞች የሴቶችና የወንዶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ቀ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች በየደረጃው ለሚገኙ ግብር ከፋይ ሴቶች በግብር ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጣቸውማድረግ፤

(በ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች ለሥራቸው የሚገለገሉባቸው የሥራ ቅፆችና ቼክሊስቶች ሲዘጋጁና ሲቀረፁ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ እንዲሆኑ ማድረግ፤

(ተ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ በሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የሚቋቋሙ ግብረ-ኃይሎችና ኮሚቴዎች የሴቶችን ተዋፅኦ ትኩረት እንዲሰጡበት ማድረግ፤

(ቸ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በሴት ሠራተኞችና በግብር ከፋይ ሴቶች ላይ የሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶችና ትንኮሳዎች የሥነ-ምግባር ችግር መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ፤

(ጎ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የሚያዙ የሥራ፣ የሰው ሀይል፣ሥልጠናና የግብር ከፋይ መረጃዎች በፆታ ተለይተው እንዲደራጁና እንዲያዙ ማድረግ፤

(ነ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የሴትና ወንድ ሠራተኞችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ፤

(ኘ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የሚጠኑ ጥናቶች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በማካተት እንዲጠኑ ማድረግ፤

(አ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ የሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የሚገኙ ሴት ሠራተኞች ለተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚያስፈልጋቸውን የሙያ ብቃትና ክህሎት ለማሳደግ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ከ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ በሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የሴት ሠራተኞችን የመረጃና ቴክኖሎጂ የዕውቀትና የአጠቃቀም ክፍተታቸውን በመለየት ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

(ኸ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ በሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የግብርና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ለማሻሻል ምርጥ ተሞክሮዎች ሲቀመሩና ሲስፋፉ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ፤

(ወ) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በስሩ በሚገኙ የሥራ ሂደቶችና ቡድኖች የግብር ከፋዮች መረጃ በደረጃና በፆታ ተለይቶና ተተንትኖ እንዲደራጅና እንዲያዝ ማድረግ፤

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ

በየደረጃው የሚገኙ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ይህንን መመሪያ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤

14. የጋራ መድረክ

የባለሥልጣኑ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪዎች የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት፣ በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበት ሁኔታ ለማመቻቸት የጋራ መድረክ እንዲዘጋጅ ያደርጋል።

15. የተሻረ መመሪያ

ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የነበረው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ማካተቻ መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ.........ቀን 2009 ዓ.ም

ከበደ ጫኔ

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር